የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን
ዓለም አቀፍ ማሕበር
WORLD ASSOCIATION OF PARISHIONERS OF E.O.T. CHURCH
4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044 - www.eotcipc.org
miimenan@yahoo.com; (214)703 9022

መጋቢት 9 ቀን 2003 ዓ/ም

ለ..........................................................................................

ጉዳዩ፤ ስለ 2ኛው ዓለም አቀፍ የምእመናን ጉባኤ፤

መንፈሳዊ ሰላምታችንን በማክበር እየገለጽን፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር 2ኛ ጉባኤ፤ መስከረም 19- እና 20 ቀኖች፤ 2004 ዓ/ም (September 30 and October 1, 2011) ዋሺንግተን ዲ.ሲ. በምትገኘው ርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስለሚከናወን፤ የጉባኤው ተሳታፊ እንድትሆኑ/እንዲሆኑ ግብዣችንን በትሕትና እናቀርባለን።

ስለ ጉባኤው ዓላማና ስለሚያተኩርባቸው አርእስቶች ከዚህ ጋር የተያያዘውን መግለጫ እንዲመለከቱ እናሳስባለን። የጉባኤውም ዝርዝር ተያይዞ ቀርቧል።

በዚህ አጋጣሚም፤ የምእመናን ማሕበር ዋና ዓላማው በቤተ ክርስቲያናችን ፍቅር፤ ሰላም፤ አንድነትና እድገት ተጠናክሮ እምነቷና ትምሕርቷ በዓለም በሙሉ እንዲስፋፋ ለማድረግ መሆኑን እንገልጻለን። ለበለጠ ግንዛቤ፤ www.eotcipc.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ መመልከት ይቻላል።

ጉባኤው በተሳካ ሁኔታ ተከናውኖ ለቤተ ክርስቲያናችን ተጨባጭ ውጤት እንዲገኝ በሚደረገው ከፍተኛ ጥረት የደብሩ የሰበካ ጉባኤ ወይም የቦርዱ አንድ ተወካይ/የርስዎ መገኘት ወሳኝ በመሆኑ ጉባኤው ላይ እንዲገኙልን እንማጸናለን። በተጨማሪም፤ ለጉባኤው መሳካት፤ የተቻለውን ያህል የገንዘብ አስተዋጽኦ፤ ከዚህ በታች በተመለከተው አድራሻ እንዲለገሡን በማክበር እንጠይቃለን።

World Association of Parishioners of E.O.T. Church
Bank: Wells Fargo
Account No: 9167531723
Routing No: 111900659
Bank Address: 13050 Coit Road, Dallas, TX 75240, USA

ስለ ጉባኤው ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ፤ የአዘጋጅ ኮሚቲውን ሊቀመንበር፤ ዶር. አክሊሉ ሐብቴን በቴሌ/ቁ (301)564 9192፤ ጸሓፊውን፤ አቶ ታደሰ ሙላትን በቴሌ/ቁ (243)423 8841 ወይም በtadskmariam@yahoo.com፤ እንዲሁም ከማሕበሩ አመራር አባሎች፤ በአድራሻችን ከተመለከተው በተጨማሪ፤ ቀኛዝማች/ዶር. ሰሎሞን አበበን፤ በቴሌ ቁ (214)697 8928 ወይም በthe_negus@yahoo.com; አቶ ኢዮኤል ነጋን በቴሌ ቁ (469)855 8488 ወይም በeyoelnega@yahoo.com; አቶ ብንያም ሙሉጌታን በቴሌ/ቁ (650)906 8012 ወይም በbmulugeta1020@gmail.com፤ እና ዶር. ወ/አማኑኤል ፈለቀን በ(507)252 1376 ወይም በamanuelfeleke@gmail.com መጠየቅ ይቻላል።

ቸሩ አምላካችን በምሕረቱና በጸጋው ጉባኤያችንን ባርኮ ለቤተ ክርስቲያናችን ለዘለቄታው የሚጠቅም ውጤት ለማስገኘት እንድንችል ይርዳን። አሜን።

ከአብሮት ሰላምታ ጋር፤

ኪዳኔ ዓለማየሁ
ሊቀመንበር